# ከአንጀት ካለቀሱ ልብ አይገድም !

የአንድ ሕዝብ ማንነትና ለመኖር ወይም እንደ ማህበረሰብ ለመቀጠል ዘርፈ ብዙ የፖለቲካ፤የኢኮኖሚ፤ማህበራዊና ባህላዊ ቁሳዊ የሆኑ ጠንካራ መሰረቶችን ይዞ ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ እሴቶችን ተግባራዊ ማድረግ ሲችል ብቻ እንደሆነ የማህበራዊ ሳይንስ (ሶሲዮሎጂ) ጥናቶች የሚያመላክቱት ከሰው በጋብቻ ልጆች በማፍራት ወደ ቤተሰብ፤ ከዛም በስጋና ደም ትሥስር ዝምድናን፤ ቀጥሎም በደጉና ክፉው አብሮ ወደ መተሳሰብና መረዳዳትን መሰረቱ ወዳደረገው ስብስብ ወይም ጎሳ፤ ይህን ተከትሎም በጋራ የመኖሪያ አካባቢ ላይ መስፈርንና የእኛ መሬት (አገር) ስሜትን በመፍጠር በሌሎች እንዳይደፈር ነቅቶ መጠበቅን፤ የህልውና ምንጭ የሆነውን አገርበግልና በጋራ በመመካከር መንከባከብንና ማልማትን፤ የኔና የእናንተ ነው ለባእድ አሳልፈን ከሰጠን ዘራችን ይበክናል የሚል የወል አስተሳሰብን የመውለ ድና ማሳደግን፤ ወዘተ. ልቦናና ሕሊና ለረጅም ዘመናት በማጎልበት ወደ ብሔረሰብ ይሸጋገራል።

አማራ የምንለውም ሕዝብ እውን የሆነው በዚሁ ሂደት እንጂ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ አይደለም። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በቁጥር ወደ ዘጠና ከሚጠጉት ማህበረሰቦች መካ ከል ከጥንት አንስቶ በግሪክ፤ በሮም፤ ከዛም በፊት በሕንድና ቻይና በነበሩ ስልጣኔዎች ሳይቀር ከተገኙ የጽሁፍ ማስረጃዎች እንደ አማራ ጎልቶ ተጠቃሽ የሆኑ እጅግ በጣም ጥቂት እንደሆኑ ከታሪክ እንማራለን። ካርታ መነደፍ ከጀመረበት ግዜ ጀምሮም ቢሆን የአባይ ሸለቆንና ጣናን፤ አሁን በሱዳን ያሉትን እንደነ ከሰላ የሚባሉ ቦታዎችን፤ ሙሉ በሙሉ ሸዋን፤ ከበሺሎ ማዶና አሸንጌ ሀይቅን፤ የከሰም በረሀን ጠቅሎ ወዘተ. አማራ ተብሎ ይጠራ እንደነበር ማስረጃዎቹ ቁጥር ስፍር የላቸውም።

አማራ በመኖሩም አማርኛ እንደሚነገርም መተረኩ አስፈላጊም አይደለም። ብቻ ለማ ንኛውም ሌላውን ትተን ሀቁን ከተመለከትን በአክሱምም ሆነ በላሊበላ የመንግስት ቋ ዋንቋዋ የነበረው አማርኛ ነው፡ አይደለም የምትሉ ካላችሁ ታሪካዊና ተጨባጭ ማስረጃ አምጡና አሳዩኝ፡፡ ይህ ማህበረሰብ ኢትዮጵያ በምትባለው አገር ደሙንና አጥንቱን ከስ ክሶ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር አብሮ ደፋ ቀና ብሎ ዘመናዊ መንግስታዊ አስተዳደር፤ ሕ ግና ደንብ የሚመራት፤ ዳር ድንበርዋ የታወቀና ልእልናዋ የተከበረ ነጻ አገር እንድትሆን

ጉልህ ሚና ተጫውቶአል፡፡ ይህንንም አሌ የምትሉ ዘመናይ ስላላችሁ በእናንተ የፈጠራ አገላለጾች አማራው ወደ ሁዋላ የሚል እንዳይመስላችሁ።

በመቀጠልም አማራ ነኝ ከሚልና ከምትሉ ጋር በግልጽ የማነጋግራችሁን ልብ በሉና አድምጡኝ። ጉድና ጭራ ከበስተሁዋላ . . . እንደሚባለው የዚህ ሁሉ ታሪክ ባለቤት የሆነው አማራ አሁን ባለንበት ዘመን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል ብለን ስንጠይቅ ፈልገንና አፈላልገን የምናገኘው መልስ አስደንጋጭ ይሆንብናል። እስቲ በተረጋጋ መንፈስ ስሜታዊ ሳንሆን ቅኝት እናድርግ፡ ተከተሉኝ -፡

ባለፉት 25 አመቶች ውስጥ ከራሱ ከአማራው አብራክ የተወለዱ ምሁሮች (ሁሉም ሳይሆኑ ታዋቂ ነን የሚሉት) ከነደፈናው ወይም ከናካቴው አማራ የለም ብለው አልተ ኮፈሱምን?

ሕወሐት ማእከላዊ ስልጣን ከጨበጠ ማግስት የተፈጠረውን የጎጠኝነት አባዜ ተጠቅ መው በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች አማራውን ሲያስመቱት ሁኔታውን ህግ ለማሰኘት የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት ሲመሰረት እነዚሁ ምሁሮች አይንህ ላፈር ብለውት በወያኔ አላስዋጡትም?። ይታያችሁ ሌሎቹ በየጎሳቸው ሲደራጁ “በርቱ” የሚሉት የአ ማራ ምሁሮች “አማራው ኢትዮጵያዊ ስለሆነ በጎስ አይደራጅም” እያሉ ራሱን ከጥፋት እንዳይከላከል እርቃኑን አላስቀሩትም? ለመሆኑ የተቀሩት በማንነታቸው ዙሪያ እንዲደ ራጁ እነዚህ ታዋቂ ምሁሮች የደገፉበት ምክንያት ሌሎቹን ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም ለማለትስ ይሆን?

የቦታዎችን የስም ዝርዝር ሁሉም ሰው የሚያውቃቸው ስለሆነ ልለፈውና ለመሆኑ በዛ ሬዋ ኢትዮጵያ አማራው መጤ ነህ ወጊድ ተብሎ ያልተመታባቸው ቦታዎች አሉን? የአማራ ክልል ተብሎ በተሰየመው ውስጥ ሳይቀር ቅማንት፤ አዊ፤ ዋግ፤ ኦሮሞ፤ አርጎባ ወዘተ. አይደለህም እየተባለ ይገደል፤ ንብረቱ ይወድምና ይፈናቀል የለምን? ለሱዳን መሬት ተሰጠ አይደለም፡ ደግሞ በሰሜን በኩል ትግራይ፡ በምራብ ቤኒሻንጉል፤ በስተደቡብ ኦሮም እንደዚሁም በስተምስራቅ አፋር በየግዜው አማራ ክልል ከሚባለው መሬት እየቆረሱ የራሳቸው ያደርጉ የለምን? እዚህ ላይ ተማር ሆኜ የክልሉ መሪ የነበሩት አቶ አዲሱ ያሉትን ላስታውሳችሁ፡ ጉዳዩ በሰሜን ሸዋ በስራ ጉብኝት ላይ ሆነው ሕዝብ ሲያወያዩ አንድ አዛውንት ብድግ ብለው " መሬታችን በቅምብቢት በኩል ወደ አርሞ የሄደበት ምክንያት ምንድር ነው?" ላሉት አቶ አዲሱ "አይ አካባቢውን የኦሮሚያ

አመራር ለማልማት ስለጠየቁ በነርሱ በኩል ቢካተት ይመረጣል በሚል ልማታዊ መንግስታችን ውሳኔ ሰጥቶበታል።" የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት። ታዲያ በዝያን ወ ቅት ደፋሩን አዛውንት ደግፎ በተቃውሞ የተነሳ የሰሜን ሸዋ የስብሰባው ታዳሚም ሆነ የቅምብቢት አማራ ነበረ ወይ? አልነበረም።

አዎ! ሁላችንም እናውቃለን አማራው በአሁኑ ዘመን ወኪል የለውም ግን ሕወሐት የተባለው ዘረኛ ቅኝ ገዢ ብ አ ዴ ን የተባለ ቅጥረኛውን አማራው ላይ ጭኖበት በ ቡችላው እንደ ካንሰር ሰርስሮ እየገደለው ሲጉዋዝ አማራው በለከፈው በሽታ ከመማ ቀቅ በስተቀር በቃኝ ሲል ይታያልን? ከፍ ሲል ያቀረብኩት ማስረጃ አማራው በማንነ ቱና በመሰረታዊ ጥቅሞቹ ላይ ያለው የወል የሆነ ግንዛቤ በማይንጸባረቅበት ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለማስመር ፈልጌ ነው።

አንድ ማህበረሰብ መመኪያና መካሪ አዛውንቶች፤ አስተባባሪ የሀይማኖት ሰባኪዎችና መምህሮች፤ መመኪያና አዲስ ጉልበት የተላበሱ ወጣቶች፤ የቤተሰብ አስተባባሪና የፍ ቅር ምንጭ እናቶችና ተቆርቋዋሪና አደራጅ ምሁሮች ያስፈልጉታል። ትግሬውን፤ ኦሮ ሞውን፤ ሲዳማውን ወዘተ. ተመልከቱ በሁሉም ረገድ ማህበረሰባቸውን የሚያሙዋሉ በትን እሴቶች ገንብተዋል፡ ታዲያ የአማራው ጉዳይ ለምን ባዶ ሆኖ ቀረ?

አንዳንድ ሰዎች “ የወደቀ ዛፍ ምሳር. . . “ በማለት አማራው መሰረቱ እንዳልተናጋ አድርገው “ እከሊትና እከሌ እኮ በተናጠል ይህን ያደርጋሉ ግን የሚድያ ሽፋን ስለ ማያገኙ. . .” በሚል ለመሸፋፈን ይሞክራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከሁሉም የከፋ አደገኛ አመለካከት ነው። አንድን ሰው “አንተ አመዳም ነህ ካላሉት ፊቱን በቅባት አያወዛም” ለነገሩ ችግሩን የምንደብቅለት ከሆነ አማራው እንዴት አድርጎ ሊነቃ ይችላል?

ጎንደር ውስጥ ሲወርድ ሲዋረድ አማራው ከጉልቱ አገርህ አይደለም ተብሎ ሲፈናቀል ሌላ ባለግዜ ወራሪ ሲረግጠው ዝም በሉ ነው የሚባለው? ወይስ ምን እናድርግ መላ ካ ልፈጠርን መጥፋታችን ነው ብሎ ሕዝብን እንዲነሳ መቀስቀስ? የትኛው ያዋጣል? በዚ ህ ረገድ ወልቃይቶች የሚያደርጉትን ይፋዊና ፍርሀት ያልተላበሰውን ትግላቸውን አደን ቃለሁ። ለመሆኑ የተቀረው ጎንደሬ መቼ ነው ከእነርሱ ጎን ተሰልፎ ባደባብይ ያበጠው ይፈንዳ ብሎ የሚነሳው? በኔ አመለካከት ይሄ ሆኖ ቢሆን ዛሬ ወልቃይት፤ጠገዴና ጠ ለምት ነጻ በሆኑ ነበር፡፡ ሶስት መቶ ሺህ የማይሞላ ቅማንት ሶስት ሚሊዮን ወይም አስር

እጥፍ የሆነውን የጎንደር አማራ ቅስም ሰብሮ መሬቱን ሲቀማው ያልተንቀሳቀሰ ማህበ ረሰብ በቁሙ አልሞተም ማለትስ ይቻላል? ግን ምን ያደርጋል . . . ታዲያ አማራው እንደ ማህበረሰብ እንዴት በዚህ መጃጃል ሊዘልቅ ይችላል? አንዳንድ አማሮች በዚህ በከረረ ሀቅ አገላለጼ እንድሚኮንኑኝ አውቃለሁ፡ ግን ያበጠው ይፈንዳ እውነቱን ተና ግሬ ከመሸበት አድራለሁ።

በአዲስ አበባ፤ በሸዋ፤ በጎጃም፤ በወሎ ወዘተ. ውጪ ያለውን አማራ ጨምሮ እንደ አንድ ማህበረሰብ በማሰባ መንቀሳቀስ ከተሳነው የወደፊቱ የአማራ እጣ ፋንታ በተአምር የሚ ስተካከል ይመስላችሁዋል? አንድ ጣት ሲቆረጥ አጥንት ውስጥ ገብቶ የሚሰማንን ህመ ምና ስቃይ አስቡት፡ ወልቃይት ወዘተ ሲነካ ሌሎቻችን ምን ቸገረን ካልን አማራው ወ ዴት እያመራ ይሆን?

ወቀሳና ትችትን መቀበል ካልቻልን እንዴት መግባባት ሊመጣ ይሆን? ለዚህ ነው አማ ራ ነኝ ብሎ የሚያምን አዛውንት፤ ምሁር፤ ወጣት፤ ሴት፤ የሀይማኖት አባት፤ ወዘተ. ራሱን መመርመር አለበት የምለው። ድርጅት ኖረ አልኖረ አንድ ህዝብ የመኖርና አለ መኖር ገደል ውስጥ ሲገባ የሲቃ ጉዳይ ብቻ ይዞት እጁን ለምን የሚጨፈጭፉት ላይ አያነሳም? ዝም ብሎ መታረድ፤ ዝም ብሎ መፈናቀል፤ ዝም ብሎ ንብረትን መቀማት፤ ዝም ብሎ አይኑ እያየ የቅም ቅም አያቶቹን መሬት ማዘረፍና የበይ ተመልካች መሆን፤ ይህ ሁሉ ለአማራው ማህበረሰብ ምን ማለት ነው? በደል የሚፈጽሙት እኮ እንደ እርሱ አንድ ግዜ ተወልደው አንድ ግዜ የሚሞቱ ናቸው፡ ፍርሀቱ ለየትኛው አለም ነው?

አይ እንዲህ አይነት ሀቅ በአማራው ማህበረሰብ ላይ እየታዩ አይደሉም በማለት ራስን ማታለል አማራውን የበለጠ ከድጥ ወደ ማጡ ያስገባዋል። ወያኔ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ትግበራ ላይ ገና መንቀሳቀስ ሳይጀምር በመሪዎቹ አደባባይ ላይ ወጥቶ "የለም ፕላኑ ተሰርዝዋል" እስከማለት ያደረሰውና በተሸናፊነት እጁን ያሰጠው የኦሮሞው ምሁር፤ ወጣት፤ ሴትና የሀይማኖት አባቶች ባንድነት ሆ! ብለው ስላመጹ አይደለምን? ታዲያ አማራው ከዚህ ምን ሊማር ይገባል? አሁን ላይ የሚፈለገው የአማራውን ድክ መት አለባብሶ በመሸፋፈንና ራስን ተአምር ይመጣልኛል ብሎ መደለል ሳይሆን ያበጠው ይፈንዳ በሚል ወኔ እውነቱን በመናገር፤ ያለማቁዋረጥ አማራው እስኪነቃ መጎትጎትና ያለበትን ያመለካከትና ግንዛቤ እጦት “አሀ ለካም ይሄ አለ “ ብሎ ራሱን በመጠየቅ ለሕልውናውና ለወደፊቱ የአማራው ትውልድ ቀጣይነት ደንዳና መሰረት ጥሎ እንዲ ያልፍ ከመወትወትና ማስተማር በቀር ሌላ አማራጭ ምን ይኖራል?

ሁላችንም የምንሞጫጭረው ለአማራው ተቆርቁረን እስከሆነ ድረስ ከአማራው ጠላቶች ትምህርት ወስደን በዚህ ረገድ ሞረሽ፤ መላው አማራ፤ ወልቃይቶች፤ ቤተ አማራ፤ ጎሕና የመሳሰሉት የአማራ ወገንተኛ የሆኑ ስብስቦችን አይዞአችሁ እያሉ ማበረታትት በራሱ የአማራ አድን ስራን ሀ ሁ ብሎ የሚያስጀምረን ስለሆነ እስቲ ፊታችንን በንቃትና ከልባ ችን ወደ እነርሱ ማዞር እንጀምርና አማራን ሊታደግ የሚችል ተቀባይነት ያለው ቀጣይ አደረጃጀት ለማምራት አንድ!ሁለት!. . . እያልን እንራመድ ።
አብነት ነኝ !!